## የድንገተኛ ክፍል ከተጠቀሙ፡-

የሐኪምዎን ስምና ስልክ ቁጥርም ይዘው ይሂዱ። ለድንገተኛ ክፍል አስታማሚም የሚወስዷቸው መድሓኒቶችና ያለብዎትም ሕመም ስሙ ምን እንደሆነ ይንገሩ።
ወደ ድንገተኛ ክፍል የሚኬድና የማይኬድባቸው ሁኔታዎች

### መሄድ አለመሄድ

- ለመወዣበርና ለአእምሮ መሳት
- የጆሮ ሕመም
- የዓጥንት ስብራት
- የፀሓይ ግርፋት
- ደም መሳልና መትፋት
- ጉንፋን፣ ሳል፣ ፍሉ
- ድንገተኛ ስቃይና የጸና ሕመም ወለምታ

### የፊት፣ የእግርና፣ የእጅ ስሜት ሲጠፋ ክትባት

- የጭንቅላት አደጋ
- የጕረሮ መሻከር
- ለከባድ የእሳት መቃጠል
- ቀላል የእሳት መቃጠል
- አደጋ ለደረሰበት ሕፃን
- የአለርጂ መርፌ ለመወጋት
- ለደረት ሕመም የፍሉ መርፌ ለመወጋት

In case of emergencies call 911:




ይህ በስደተኞች መቋቋሚያ የጤና ክፍልና በሰብኣዊ አገልግሎት ቢሮ ከተገኘው ገንዘብ የተዘጋጀ ጽሑፍ ነው።

**CONTACT INFORMATION:**
riht@uscridc.org
U.S. Committee for Refugees and Immigrants
1717 Massachusetts Ave., NW
Suite 200
Washington, DC 20036
Phone: 202 • 347 • 3507
Fax: 202 • 347 • 7177
www.refugees.org

* * * Translated by G. E. Gorfu & Asc.



## ይኽ ጽሑፍ በስደተኞች ማቋቋሚያ ቢሮ ገንዝብ፣ ከአሜሪካ የጤና ክፍልና የሰብኣዊ አገልግሎት ተዘጋጀ።

(ER- Amharic)

U.S. COMMITTEE FOR REFUGEES AND IMMIGRANTS
USCRI
www.refugees.org
*Protecting Refugees, Serving Immigrants, Upholding Freedom since 1911*

# HEALTHY LIVING

## የጤና አገልግሎት በአሜሪካ
## በአሜሪካ የጤና አገልግሎት በተለያዩ መንገዶች ለማግኘት

ሲቻል፣ ዋና ሆነው የሚጠቀሱት የሚከተሉት ናቸው:-

- ከሓኪም ቢሮ በመሄድ
- የአስቸኳይ አገልግሎት ጣብያ ("ተራምዶ ግብት" በመባል የሚታወቅ)
- የድንገተኛ ክፍል

### ከሓኪም ቢሮ የምሄደው መቼ ነው?

ከሓኪም ቢሮ ለመሄድ አስቀድሞ ቀጠሮ ተይዞ፣ ቋሚ ሓኪምዎን ለማየት ሲሆን፣ ቀጠሮ የሚያዘው ለሚቀጥሉት ዓይነት ሕመሞች ነው:-

- ጉንፋንና ፍሉ (ኢንፍሉዌንዛ)
- የጆሮ ሕመም
- የአለርጂ መርፌ ለመወጋት
- ለክትባት
- ለዓመታዊ መላው አካላት ምርመራ

### የአስቸኳይ አገልግሎት ጣብያስ የሚያስፈልገኝ መቼ ነው?

የአስቸኳይ አገልግሎት ጣብያ ወይም "ተራምዶ ግብት" የሚባሉት ልክ እንደ ሓኪም ቢሮ ሲሆኑ፣ ልዩነታቸው ምንም ቀጠሮ የማያስፈልጋቸው በመሆኑ ብቻ ነው። ግን ቋሚ ሓኪምዎ ሳይሆን፣ የዕለቱ ተረኛውን ሓኪም ነው የሚያዩት። አስቸኳይ አገልግሎት የሚሰጡ ክሊኒኮች ብዙውን ጊዜ ከሆስፒታል ወይም ከታላላቅ የሱቆች መደብር አጠገብ በመገኘት፣ ከጥዋት ማለዳ አንስቶ እስከ ምሽት ድረስ ክፍት ናቸው። አስቸኳይ አገልግሎት ለቀላል ሕመሞችና ጉዳቶች፣ ማለትም:-

- ለጆሮ ሕመም
- ለፀሓይ ግርፋትና ለቀላል የእሳት መቃጠል
- ለጉንፋን፣ ሳል፣ ፍሉ
- ለቀላል ትኩሳት
- ለትምህርት ቤትና ለሥራ የሙሉ አከላት ምርመራ ማስረጃ ሲያስፈልግ
- የአለርጂ መርፌ ለመወጋት

### የድንገተኛ ክፍል የሚያስፈልገኝ መቼ ነው?

የድንገተኛ ክፍል ወይም "ኢ.አር" የሚባለው የሚገኘው በሆስፒታል ነው። ሃያ አራት ሰዓት፣ ሰባቱም ቀናት ክፍት ነው። የድንገተኛ ክፍል ዋጋ ከሓኪም ቢሮና ከአስቸኳይ የአገልግሎት ጣብያዎች በጣም የተወደደ ነው። ወደ የድንገተኛ ክፍል ከሄዱና ሕመምዎ አስጊ ካልሆነ ብዙ ወረፋ መጠበቅ ይኖርብዎት ይሆናል። ወደ የድንገተኛ ክፍል የሚሄዱት አደጋ ሲደርስና አጣዳፊ ሕመም ሲይዝዎት ብቻ ነው። ለምሳሌ:-






- የደረት ሕመም፣ ከፊትዎ፣ ከእግርዎ፣ ከእጅዎ የመደንዘዝ ስሜት
- የአንደበት መዘጋት ችግር ሲኖርብዎት
- ከፍተኛ ትኩሳት ከአንገት መድረቅ ጋር
- የአእምሮ መወዣበር፣ የመተንፈስ ችግር
- ከባድ የትንፋሽ ማጠርና ለመተንፈስም መጣጣር
- የመርዝ
- ድንገተኛ የአእምሮ መሳት
- የደም መሳል፣ ወይም መትፋት
- ድንገተኛና አዲስ፣ የማያውቁት ከባድ የሕመም ስቃይ ሲሰማዎት